22140011

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A: LITERATURE – STANDARD LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A : LITTÉRATURE – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A: LITERATURA – NIVEL MEDIO – PRUEBA 1**

Friday 9 May 2014 (morning)
Vendredi 9 mai 2014 (matin)
Viernes 9 de mayo de 2014 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a guided literary analysis on one passage only. In your answer you must address both of the guiding questions provided.
- The maximum mark for this examination paper is *[20 marks]*.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Rédigez une analyse littéraire dirigée d'un seul des passages. Les deux questions d'orientation fournies doivent être traitées dans votre réponse.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d'examen est *[20 points]*.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un análisis literario guiado sobre un solo pasaje. Debe abordar las dos preguntas de orientación en su respuesta.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es *[20 puntos]*.


© International Baccalaureate Organization 2014

https://xtremepape.rs/

*ከሚከተሉት ምንባቦች **አንዱን** መርጠህ ስነጽሁፋዊ ትንታኔ ስጥ:: ከታች የተቀመጡትን ጥያቄዎች መመለስ ይኖርብሀል::*

**1.**

ለነፍሳት ሲጥሲጥታታ- ቀልቡን የገበረው፣
የፈጣሪ መዳፍ - ቁራሽ ነኝ የሚለው፣
በክብ ሩጫ ውስጥ - ዘላለምን ቃኝቶ - ዘላለም የሆነው፣
ባበጀጃት አለም - በምናብ የሚኖር - ባለቅኔ ዕብድ ነው::

መድረሻ በሌለው - ረጅም ጎዳና፣
ፍጻሜ አልባ ተጓዥ - ፍኖቱ የቀና፣
እንደ አይን ርግብታ - አፍታና ቅጽበት ነው፣

ሆኖም በዚች ዕድሜ - እእርሱ ዘላለም ነው፣
በዚህ ዘላለም ውስጥ - ባለቅኔ ዕብድ ነው::

ባለቅኔ ዕብድ ነው!!
አሁን አቀማጥሎሽ - "የአይኔ አበባ" ብሎሽ - ይወረወርሻል፣
ጠልቶሽ - እእንዳይመስልሽ - ውሀና እሳት ነው - ሲነጋና ሲመሽ::
አቅርቦ ሲጠላሽ - አርቆ ሲወድሽ፣
አንድ ጊዜ ረግረግ - አንድ ጊዜ ጭንጫ ልብ - ሲሆን የምታይው፣
ጠልቶሽ … እንዳይመስልሽ፣
ወዶም … እንዳይመስልሽ፣
ባለቅኔ እእንዲህ ነው ሲነጋና ሲመሽ::

ባለቅኔ ዕብድ ነው!!
ከንፋስ፣ ከቁር… ከውርጭ የሚጣመር፣
ከእሳት፣ ከአፈር ፣ከሰማይ የማመክር፣
ከህዝብ ተፋቅሮ - ከራሱ የሚጣላ፣
ከራሱ ተማክሮ - ከሌላ የማይገጥም፣
ባለቅኔ እእንዲህ ነው!!

በንዴትሽ አብራክ - ፊትሽ ሲንቀጠቀጥ፣
የቅንድብሽ መርገፍ - በእምባ ሲረጥብ - ሲርስ ሽፋሽፍትሽ፣
እምባሽ ጎርፍ ሲሆን - ሲንኳለል በጉንጭሽ - ሲያቋርጥ ባ'ንገትሽ፣
ዕብዱ ባለቅኔ!!
ስላ'ባይ ያስባል - "አገሬ ስታለቅስ - ምን ይመስል" ይላል::
ከመስኖ፣ ከጅረት፣ ከወንዝ ይፋቀራል፣
ያ'ገሩ እምባ ብዛት - ከእምባ ያወዳጀዋል::
ስላንቺ ይረሳል!
ስለ'ሷ ይሳሳል!
… ወንዝ ሆኖ ይፈሳል!!



https://xtremepape.rs/

ያኔ ኢምንት ልብሽ …
ከተስፋ ተጣልታ፤ ንዴቷን ተንጣ … “ዱብ እንቅ” ስትይ፤
እልህ እእሳት ሆኖ፤ እንደ ትኩስ ሽሮ … ቱግ ቱግ ሲያደርግሽ፤
እሱ ሩቅ አስቦ፤ የተፈጥሮን ስ’ራት … ይመረምር ይዟል፤
ከምድር ማህፀን … ነውጥ የተነሳ’ለት፤
እሳተ - ጐመራ … ያለውን መፍለቅለቅ፤
ባንቺ ውስጥ ያልማል!
ባለቅኔ ዕብድ ነው - ከብደቱ ሲታረቅ አይችልም ማባበል።

አንዱ አለም አባተ፣ *ፍቅርና መዳፍ*፣ (2011)።

(a) በግጥሙ ስለቀረበው መልእክት ያገኘሽው ግንዛቤ ምንድነው?

(b) ፀሀፊው የተጠቀመባቸው ቴክኒኮች የግጥሙን መልእክት ለማጎልበት የነበራቸውን አስተዋጽኦ አስረዳ።



https://xtremepape.rs/

**2.**

ከልጃገረዶቹ አንዷቱ ለአያሌ አመታት በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የርስት ክፍል ሹም የነበሩት የአቶ አንዳርጌ ሴት ልጅ ቀፀላ አንዳርጌ፤ በተሳተፈችባቸው ትርዒቶች ሁሉ "የኮከቦች ኮከብ" ለመባል የበቃች ግምባር ቀደም አርቲስት ነበረች፡፡ ይህም በአነጋገር ችሎታዋ፤ በአቀራረብ ስልቷና ከሊቁ ደራሲ ባጠናቸው ጣፋጭ ዝማሬዋ ማራኪነት ብቻ ሳይሆን፤ ከተፈጥሮ ፀጋ በታደለችው አይን አገላለጧ፤ ብሩህ ጠይም መልኳ፤ ሙሉ ቅርፅ አካሏና ጠቅላላ አንቅስቃሴዋ የዕድምተኞችን አይን የሚስብ ልዩ ጠባያዊ ተሰጥኦ ስላጐናፀፋት ነበር፡፡

ሌላይቱ ጉብል ደግሞ በአንዱ ትርዒት ላይ "እመየት ቸኮለች" የሚል ስም ተሰጥቷት እንደጠጅ ኮማሪት ሆና ስትጫወት፤ የሐር ነዶ መሳይ ክምር ጎፈሬዋን በደንብ አበጥራ፤ በጥበብ ኩታና በሽብሽቦ ቀሚስ ሽቅርቅር ብላ ሳብ-ረገብ ባለው ሽንጥና ዳሌዋ እያረገረገች በጠጪዎች መሐል ሽር-ጉድ በማለት፤ አይነገብ አይኖችዋን ግራና ቀኝ ሰረቅ፤ ነጫጭ ጥርሶችዋን አንዳንድ ጊዜ ፍልቅ እያደረገች ስትሽኮረመም ፍጹም የአራዳዋን የነጋድራስ ቀፀላ የልጅ ልጅ መስላ የታየችው አሰለፈች ማሞ ነበረች፡፡ በሌላው መድ ረክ ላይ ከቅዱሳት እንስት አንዷን ተመስላ በቀረበች ጊዜ፤ እእንደወንጌሉ ቃል ራሷን ሸፍና፤ እስከእግር ጥፍሯ ድረስ የተዘናፈለ የጥንቱን የአገር ልብስ ግርማ ተጎናጽፋ፤ ምዕመናንን ሁሉ በታላቅ ትህትና ታ ስታገለግልና ድኩማን ነዳያንን በርህራሄ ስሜት ከልብ ስትረዳ የተመለከተና፤ በለስላሳ ድምጿ የምታፈ ልቀውን መንፈሳዊ ቃላት የሰማ ሰው ሁሉ፤ ሁለቱንም ተውኔት በተለያየ ጠባይ የተጫወተችው አንዷቱ አሰለፈች መሆኗን ለማመን እስኪቸገር ድረስ፤ የብልህነት ችሎታዋን በስራ ያሳየች ንቁ ባለሞያ ነበረች፡፡

እእንደነዚህ ሁሉ ጠቃሚ ካልሆነ አሮጌ ባህልና የልማድ መጋረጃ ለመውጣት ታድለው፤ ዘመናዊ ውን ትምህርት ከሚከተሉት መካከል የትያትርን ጥበብ የቀሰሙ ልጃገረዶች ጥቂቶች ስንኳ ባይሆኑ፤ የሴቱን ውድድር በዚሁ ልግታና ስለወንዶች ልጆች በጥቂቱ ላስታውስ፡፡

ከተወኔት ጓደኞቹ "የንብ አውራ" የሚል ቅጽል ስም የወጣለት (አንድአይናው) ጥሩነህ … በልዩ ልዩ ጊዜያት ለትርዒት ከቀረቡት የዮፍታሔ ዜማዎች ለሚበልጠው ክፍል ዋና አቀንቃኝ ሆኖ በመሪነት የተ ጫወተ ድምፃዊ ወጣት ነበር፡፡ ይልቁንም "የኛማ ሙሽራ"ን በተስረቀረቀ ዜማ ሲያወርዳት የሰማው ሰው ሁሉ በለዘበ ቃናው ከመመሰጡ የተነሳ፤ በአዳራሹ ውስጥ አብሮት የስሜት ዝማሜ ማድረግ ብቻ ሳይ ሆን፤ ከአዳራሹም ውጭ ዜማውን ለማጥናት ልጁም አዋቂውም በየመንገዱ ላይ የየግል ድምፁን በዜማ እእየቃኘ የለሆሳስ ዝማሬ ሲያደርግ ይታይ ነበር፡፡

ከጥሩነህ ሌላ በዮፍታሔ ትያትሮች ተጫዋችነቱ ሊጠቀስ የሚገባው በሻህ ተክለማርያም፤ ከድም ፃዊነቱ ይበልጥ በሙዚቃ ጥበብ ተሰጥዎው ስመጥር የሆነ ብልህ አርቲስት ነው፡፡ እርሱም ዛሬ "የአገር ፍቅር የባህል ሙዚቃ" በመባል የሚታወቀውን ፍጹም ኢትዮጵያዊ የሆነ ዘመናዊ የዜማ መሣሪያዎች ቅንጅት (ኦርኬስትራ) አቀናብሮ የፈጠረና፤ ህብረ ቅኝቱን በማስንቆ፤ በበገና፤ በዋሽንት፤ በአታሞ፤ በመ ለከትና በመሳሰሉት ብቻ አጣፍጦ በማቅረብ ሙዘቀኞችን ያሰለጠነ ብቸኛ ባለሞያ ሲሆን፤ አሁን እእዚህ ላይ ያቀረበው በዚያ ዘመን ከዮፍታሔ ድራማዎች አንዱ ክፍል ውስጥ ሲጫወት፤ ኢትዮጵያ በአንዲት ቆንጆ ተመስላ የጥንቱን ጀግና ድፍረትና ወኔ በወጣት ልጆች መንፈስ ውስጥ ለመቅረጽ ጥንታው ያኑን በፍቅረኛ ናፍቆት አምሳል "ና ናና… ናና ናና ናና!ና! …" እእያለች የሰቀቀን ዜማዋን በማሰማትና እጅዋን በማርገብገብ በጠቀሰችው ጊዜ፤ የጀግኖቹን መንፈስ የተመሰለው አርበኛ በሻህ እንደ መሪዋ የሚያስተጋባ ወንዳወንድ ድምጹን ዘለግ አድርጎ በመልቀቅ "ነይ! ነይ! ነይ!… ነይ! ነይ! ነይ! ነይ! ነይ፤ ነይ ነይ! ነይ! …" እእያለ በትካዜ ሲያንጎራጉር አዳማጩን ሁሉ አፍዝዞ የየግል ትዝታ ሰመመን አስይዞ ታል፡፡

በለጠ ገብሬ፣ *በእድሜ ጎዳና ላይ የጉዞ ትዝታ*፣ (2012)፡፡

(a) በቅንጭብ ጽሁፉ ውስጥ ተዋናዩ እንደምን ቀረቡ?

(b) ፀሀፊው የአንባቢው አመለካከት ላይ ተጅእኖ ለማሳደር የተጠቀመባቸው ቴክኒኮች ላይ አስተያየት ስጥ፡፡



https://xtremepape.rs/